የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፴፫
አዲስ አበባ ሰኔ ፩ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

18th Year No.33
ADDIS ABABA 8th June, 2012

<u>ማውጫ</u>

**አዋጅ ቁጥር ፯፻፵፫/፪ሺ፬ ዓ.ም**

የተሻሻለው የአፍሪካ ማሪታይም ትራንስፖርት ቻርተር ማፅደቂያ አዋጅ …... ገጽ ፮ሺ፫፻፵፬

**<u>CONTENTS</u>**

**Proclamation No.743/2012**

Revised African Maritime Transport Charter Ratification Proclamation. ... Page 6344

## አዋጅ ቁጥር ፯፻፵፫/፪ሺ፬

## <u>የተሻሻለውን የአፍሪካ ማሪታይም ትራንስፖርት ቻርተር ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ</u>

የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ጉባኤ እ.አ.አ ጁላይ ፳፮ ቀን ፪ሺ፲ በዩጋንዳ ካምፓላ ባደረገው ስብሰባ የተሻሻለውን የአፍሪካ ማሪታይም ትራንስፖርት ቻርተር ተቀብሎ ያፀደቀው በመሆኑ፤

ይህንኑ ቻርተር የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ግንቦት ፱ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

### ፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ “የተሻሻለው የአፍሪካ ማሪታይም ትራንስፖርት ቻርተር ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፯፻፵፫/፪ሺ፬” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## PROCLAMATION No. 743/2012.

## <u>A PROCLAMATION TO RATIFY THE REVISED AFRICAN MARITIME TRANSPORT CHARTER</u>

WHEREAS, the Revised African Maritime Transport Charter was adopted by the summit of Heads of State and Government of the African Union in Kampala, Uganda, on 26 July, 2010;

WHEREAS, the House of People's Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Charter at its session held on the 17th day of May, 2012;

NOW, THEREFORE, in accordance with sub-article (1) and (12) of Article 55 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

### 1. <u>Short Title</u>

This Proclamation may be cited as the "Revised African Maritime Transport Charter Ratification Proclamation No. 743/2012."

## ፪. የቻርተሩ መጽደቅ

የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ጉባኤ እ.አ.አ ጁላይ ፳፮ ቀን ፪ሺ፲ በዩጋንዳ ካምፖላ ባካሄደው ስብሰባ የተቀበለው የተሻሻለው የአፍሪካ ማሪታይም ትራንስፖርት ቻርተር በዚህ አዋጅ ጸድቋል፡፡

## ፫. የትራንስፖርት ሚኒስቴር ስልጣን

የትራንስፖርት ሚኒስቴር አግባብ ካላቸው የመንግሥት አካላት ጋር በመተባበር ቻርተሩ በስራ ላይ እንዲውል ለማድረግ የሚያስፈልጉ እርምጃዎችን የመውሰድ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል፡፡

## ፬. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ሰኔ ፩ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም**

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

## 2. Ratification of the Charter

The Revised African Maritime Transport Charter adopted by the summit of Heads of State and Government of the African Union held at Kampal, Uganda, on 26 July 2010 is hereby ratified.

## 3. Power of the Ministry of Transport

The Ministry of Transport is hereby empowered to undertake, in cooperation with the concerned governmental organs, all acts necessary for the implementation of the Charter.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall enter in to force on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 8th day of June, 2012.**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**